## በሕሊና ትግል ድል የሚነሡ ብፁዓን ጀግኖች ናቸው

**ጌታቸው ኃይሌ**

“ከሕዝቡ ጋር አብሬ ልሂድ ወይስ ልቅር?” “ተናጋሪው ከተናገረው ውስጥ ያልገባኝ ነገር አለ ። ሰው እየሰማ ፥ ልጠይቅ ወይስ ዝም ልበል?” መሄድ እፈልጋለሁ ፤ ሕሊናየ ግን ሁኔታውን እየመረመረ ፥ “ትክክሉና የሚገባህ ባትሄድ ነው ፤ ዐርፈህ ተቀመጥ ፤ ከጀሌ ጋር አትጓዝ” ይለኛል ። “ለመጠየቅ የፈለከውንም ጠይቅ ፤ ሰው ምን ይለኛል ብለህ ደንቁረህ አትቅር” ይለኛል ።

ሕሊናየን ታዝዤ ከመሄድ ብቀር ፥ ለመጠየቅ የፈልኩትንም ደፍሬ ብጠይቅ ፥ ሰው ምን ይለኛል? የለም ፥ **አልቀርም እሄዳለሁ** ፤ ሰዉ ሁሉ ሲሄድ እንዴት አድርጌ ተለይቼ እቀራለሁ? ሰው ሁሉ የሚያውቀውን ጥያቄ ብጠይቅ ፥ ሰው ምን ይለኛል? **አልጠይቅም ፤ ይቅርብኝ ።**

እውነቱና ትክክሉ አለመሄድ መሆኑን ፥ ዐርፎ መቀመጥ መሆኑን ሕሊናየ እየነገረኝ ፥ ብሄድ ምን ዓይነት ሰው እባላለሁ? ሕሊና ቢስ (ሕሊና የሌለው) ያሰኘኛል? የለም ፥ እንደሱ አይደለም ። ሕሊናማ አለኝ ፥ ያውም የሚወተውት ፤ ከዳሁት እንጂ ። “ሕሊና-ቢስ” እና “ሕሊና-ከዳተኛ” የተለያዩ ናቸው ። “ሕሊና-ቢስ” የሚባለው ወንጀል ሲፈጽም ፥ ሰው ሲያሰቃይ ፥ ሲገድል አንጀቱ ይርሳል ። “ሕሊና-ከዳተኛ” ተመሳሳይ ወንጀል ሲፈጽም ፥ አንጀቱ ይንሰፈሰፋል ፤ ምናልባትም ሲበዛበት ያብድ ይሆናል ። እናም መሆን የሚገባው ማንንም ሳልፈራ ጨክኜ **መቅረት ፥ ዐርፎ መቀመጥ ፤ ጥያቄየንም ማንንም ሳልፈራ መጠየቅ** እንደሆነ ሕሊናየ እየነገረኝ ፥ ሰው የሚለውን በመፍራት ብሄድ ፥ ጥያቄየንም ሳልጠይቅ ብቀር ፥ በሕሊና ትግል ተሸነፍኩ ማለት ነው ።

በሕሊና ትግል ተሸንፎ ማጥፋትና እርግጠኛ ባለመሆን (ባለማወቅ) መሳሳት የተለያዩ ናቸው ። ለምሳሌ ፥ አንድ ሰው መስቀልኛ መንገድ ላይ ሲደርስና የትኛውን መንገድ ይዞ መጓዝ እንዳለበት እርግጠኛ ባለመሆን ፥ የተሳሳተውንም መንገድ ቢመርጥ ባለማወቅ እንጂ ፥ ለሕሊናው ባለመታዘዝ አይደለም ፤ ሰውየው ይታዘንለታል እንጂ ፥አይወቀስም ።

በሕሊና ትግል የሚሸነፍን ሰው ግን ደካማ ነው ፤ ቁም ነገር ላይ አትፈልጉት ፤ እገሌ አለልን አትበሉ ። የማያምንበትን ያደርጋል ፤ ይከዳችኋል ። ተሸንፎ እናንተንም ከሽንፈት ላይ ይጥላችኋል ። ምሳሌ ልስጥ ፤ ወያኔዎች አዲስ አበባን እንደተቈጣጠሩ ፥ የሽግግር መንግሥት አቋቁመው ፥ ሕገ መንግሥት አጸደቁ ። ከዚያ ቀጥለው ፥ ያቋቋሙትን የሽግግር ሸንጎ ፥ “ኤርትራ ትገንጠል/ አትገንጠል?” በየሚል ጥያቄ ላይ አወያይተው ድምፅ እንዲሰጥበት ጠየቁት ። ከአንድ ሰው (ከጀግናው ከፕሮፌሰር ዓሥራት ወልደየስ) በቀር ሁሉም “ትገንጠል” አለ ። ጀግና ማለት “ተባአስ በእንተ ጽድቅ እስከ ትበጽሕ ለሞት” (ለሞት እስከምትደርስ ለእውነት ተሟገት) የሚለውን የመጽሐፍ ቃል የሚያከብር ነው ።

እንግዲህ ተመልከቱ ፤ “ኤርትራ ትገንጠል” ብለው ድምፅ ከሰጡት ውስጥ በሀገር አንድነት የሚያምኑ ፥ ቀደም ብሎ ፥ ከሻዕቢያ ጋር ይደረግ በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት እንዲያሸንፍ የሚመኙ (ምናልባትም የሚጸልዩ) እንዳለባቸው አውቃለሁ ። ሆኖም እነዚህ ሰዎች “ትገንጠል የሚል ድምፅ

ለመስጠት እጃችሁን አውጡ" በተባሉ ጊዜ ፥ የሕሊና ትግል አላጋጠማቸውም ለማለት አንችልም ። ግን ተሸነፉ ፤ "አትገንጠል" በሉ የሚላቸውን ሕሊናቸውን ከዱት ። ድምፅ አሰጣጡ እጅ በማውጣት መሆኑ ቀርቶ ፥ በምስጢር ቢሆን ኖሮ ፥ እነዚህ ሰዎች ለሕሊናቸው ታማኝነታቸውን ያሳዩ ነበር ። ጥንቱንም የምስጢር ድምፅ አሰጣጥ ሥርዓት የተቋቋመው የማያምኑበትን አሳብ የሚቀበሉትን ሰዎች ከድቀት ለማዳንና አስከፊ ውጤቱን ለማስወገድ ነው ። ግን ነፍሱን በሰማይ ይማራትና ፥ ያ ተንኮለኛ ሰው ፥ ምርጫውን በምስጢር ማድረጉ ቀርቶ "እጃችሁን አውጡ" ብሎ አፈጠጠባቸው ። በዚህ ዘዴው ሕሊናቸውን አስከድቶና የማያምኑበትን አሳምኖ ፥ ዐውቃ በፈቃዷ የመጣችውን ኤርትራ ሳታውቅ ፥ ፈቃዷ መሆኑ ሳይታወቅ አባረራት ።

የሕሊና ክህደት የተፈጸመባቸው ድርጊቶች በብዛት መጥቀስ ይቻላል ። ሌላ ምሳሌ ለመጨመር ያህል ፥ መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የሠራተኞች ፓርቲ የሚለውን ድርጅት አቋቁሞ ሀገሪቷን በኮሚኒስት ሥርዓት ሲያሰቃያት የማእከላዊው ኮሚቴ አባላት ይደግፉት እንደነበረ እናስታውሳለን ። ከዕለታት አንድ ቀን ብድግ ብሎ ለግብር አበሮቹ ፥ "ከዛሬ ጀምሮ ኢትዮጵያ የምትመራው በቅይጥ ኢኮኖሚ ነው" አላቸው ። እነዚህ ቃላት ካፉ ሲወጡ ፥ ጓደኞቹ የተሰማቸው ደስታ ወደር አልነበረውም ። ከማህላቸው አንዱ ነሸጥ ብሎት ከመቀመጫው ተነሥቶ ፥ "ክቡር ፕሬዚዴንት ፥ ይኼ ዓዋጅ ሲነገር የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅ ደስታ ይሰማዋል" ሲል ተናገረ ። ፓርቲውን ሕሊናቸውን የከዱ አባላት ሞልተውት ነበር ማለት ነው ።

ከዚያም ቀደም ብሎ ፥ የደርግ አባላት ድምፅ በመስጠት ስድሳ ሁለት ባለሥልጣኖች በጥይት እንዳስደበደቡ የማይረሳ የጉድ ታሪክ አለን ። ዝርዝሩን ስለማላውቅ ብዙ አልጽፍም ፤ ግን ጥቂቶችም ቢሆኑ ሕሊናቸውን ክደው በሰዎቹ መፈጀት የተስማሙ ሳይኖርባቸው አይቀርም ። መገደል እንደሌለባቸው ሕሊናቸው እየነገራቸው "ይሙት በቃ" ፈረዱባቸው ። ለነገሩማ ፥ መጀመሪያውኑ የደርግ አባላት እነዚህ የተፈጁት ሰዎች ባለሥልጣኖች ከመሆናቸው በቀር ስለነሱ ሌላ ምን ነገር ያውቁና ነው "ይኸም ይኸም ይሙት" እያሉ ድምፅ የሰጡት? ስንቱንስ ሕሊናቸው እንዳይገደሉ የነገራቸውን "አይገደል" ብለው አዳኑት?

ሌላ ምሳሌ ፤ ወያኔዎች "አማራው ጠላታችን ነው ፤ መጥፋት አለበት" ሲሉ ፥ ከመካከላቸው ሕሊናቸውን ክደው ፥ "አዎን ፥ አዎን ፥ ጠላታችን ነው ፤ መጥፋት አለበት" ያሉ አይጠፉባቸውም ። አንዱ አቶ ገብረ መድኅን አርአያ ነበር ። ሕሊናው ቢጨቀጭቀው የኋላ ኋላ አዳምጦት በጀግንነት ታዘዘው ። ጥሏቸው ሄደ ። እነ ሟቹና እነ ገና-ሟቾቹ የሚሠሩት ሥራ ወንጀል መሆኑን ሕሊናው በየቀኑ ሲነግረው ፥ ሕሊና ከዳተኛነት ያሰረበትን ገመድ በጣጥሶ ወጣ ።

አሁንም ቢሆን ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ በዘር ሲለያይ ከደጋፊ አባላቱ ውስጥ ሕሊናው እየወቀሰው አብሮ የሚጓዝ እንዳለባቸው አያጠራጥርም ። ማስረጃው የሕሊናቸው ወቀሳ ስለበዛባቸው ጥለዋቸው የሄዱት ናቸው ። አንዱ ኤርምያስ ለገሰ የሚባለው "የመለስ ትሩፋቶች . . ." መጽሐፍ ደራሲ ነው ።

"እንገንጠል" ከሚሉት ኦሮሞዎች መካከልም ሕሊናቸው "ተዉ ፤ አገራችሁን በዲሞክራሲ ሥርዓት አዳብሩ" እያለ ሲመክራቸውና ሲወቅሳቸው "ዝም በል" እያሉ የሚክዱት ብዙዎች ሳይሆኑ አይቀሩም ። ምስክሬ ምርጫ 97 ነው ። በዚያን ጊዜ አብዛኛው የኦሮሞ ሕዝብ የመረጠው በኢትዮጵያ አንድነት

የሚያምነውን ቅንጅትን ነው ። ግን ከሕሊና ወቀሳ ይልቅ የንቅናቄው ግፊት (“ኦሮሞ ሆኜ ዝም ስል ቀንደኞቹ ምን ይሉኛል” የሚለው ግፊት) አይሎ ስላሸነፋቸው አብረው ይጓዛሉ ።

ሕሊናቸው ፥ ኦሮሞዎች በኢትዮጵያ ታሪክ የተጫወቱትን ግዙፍ ሚና እንዲያስታውሱ ፥ አያውቁትም እንደሆነ እንዲያውቁ ይወተውታቸዋል ። ግን ይሉኝታ ፈርተው ካዱት ፤ ተሸነፉ ። ኦሮምኛን በኢትዮጵያ ፊደል መጻፍ እንደሚቻል ፥ ከመቻልም አልፎ እንደሚሻል ፥ ሕሊናቸው ይነግራቸዋል ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ በኦሮምኛ ቋንቋ በኢትዮጵያ ፊደል አምሮበት እንደተጻፈ ያውቃሉ ። ትክክሉ በዚያው ቢቀጥሉ መሆኑን ሕሊናቸው ቢወተውታቸው ፥ ቢወተውታቸው አልሰማ አሉ ። ካዱት ፤ ተሸነፉ ። ሌላው ቢቀር ፥ “እናንተ ካሥኛችሁ በላቲንም ሆነ በዐረቢ ፊደል ጻፉ ፤ መብታችሁ ነው ። እኛ ግን ኦሮምኛን ለመጻፍ እንዲቀለን ፥ ሌሎችም ቋንቋውን እንዲማሩት ለማጓጓትና ለማበረታታት ፥ በቀላሉ በአገራችን ፊደል እንጽፋለን” ብለው መነሣት አልቻሉም ። ቢችሉ በውድድር የኢትዮጵያ ፊደል ያሸንፍ ነበር ። ኦሮምኛ እንደዱሮው በኢትዮጵያ ፊደል እንዳይጻፍ የሚከለክል ሕግ የለም ። እንዲያውምኮ ኦሮምኛ ኢትዮጵያዊ ቋንቋ ስለሆነ በምን ፊደል መጻፍ እንዳለበት ወሳኙ ኢትዮጵያን የሚወክል ድርጅት እንጂ አንድ ጎሳ አይደለም ።

በሕሊና ትግል የሚሸነፍ ሰው የሕሊና ቢስ ታናሽ ወንድም ነው ። ከላይ እንዳመለከትኩት ፥ ከቁም ነገር ላይ አይገኝም ። ለትዳር እንኳን አይበቃም ፤ በቤቱ ያለለትን ትቶ ከውጪ ይቀላውጣል ። እንዲህ ያለ ሰው ፥ እንደምናየው ፥ ራሱ ተሸንፎ አገርን ከአደጋ ላይ ይጥላል ። አገር ወዳድ ነኝ የሚለው ሰው ሕሊናው “ተው” እያለው ፥ ኀይል በመፍራት ፥ ገንዘብ በመውደድ ሕሊናው የሚነግረውን ትቶ ፥ የሰው ነፍስ የሚጠፋበትን ፥ ሀገር የሚጎዳበትን አማራጭ ይመርጣል ። በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያን የሚያንገላቷት በጥላቻ ቀርጠው የተነሡ የትግራይ ልጆች ብቻ አይደሉም ። እነዚህ ወስላቶች ኀይል ያገኙት ሕሊናቸውን የከዱ ፥ ሕሊናቸው የሚነግራቸውን የማይሰሙ ሰዎች በሚሰጧቸው ድጋፍ ጭምር ነው ። ወያኔዎች “ከዛሬ ጀምሮ ጎሰኝነት ቀርቷል” ብለው ቢያውጁ ፥ ሕሊና ከዳተኞች በሙሉ ከበረት እንደተለቀቀ ጥጃ ይናጥጡ ነበር ። ሕሊናቸውን ቢከተሉ ግን ፥ በደስታ ለመናጠት የወያኔን ዓዋጅ መጠበቅ ባላስፈለጋቸው ነበር ። የኦሮሞ ፖለቲከኞችም ኦሮምኛ ለመማር ቀናውን መንገድ ያሲዙን ነበር ።

ሕሊናውን የማይከተል ሰው ደካማ ከሐዲ ነው ። በሕሊና ትግል ድል የሚነሣ ግን ጀግና ነው ።